በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 217928
ግንቦት 01 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. መምህርት ትዕግስት ተቀጸል

2. መምህርት መሬም አሚን

3. መምህርት ሻይማ ሞሃመድ

4. መምህር አብዱላዚዝ አህመድ

5. መምህር ፋሲካ ዘውዱ

ተጠሪ ፡- የመን ኮሚኒቲ ትምሕርት ቤት፡- ጠበቃ ሙባረክ አብዱሰላም ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በግል የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሥራ ውል መቋረጡ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች የስር ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በተጠሪ ትምሕርት ቤት ተቀጥረን ስንሰራ ደመወዝ በማቋረጡ በመዝገብ ቁጥር 113179 ክስ አቅርበን ደመወዝ እንዲከፈል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተወስኗል፡፡ በ2013 ዓም ስራ እንጀምራለን ብለን ስንጠብቅ ትምሕርት ቤቱን በመዝጋት በሕገ-ወጥ መልኩ ያሰናበተን በመሆኑ ካሣ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ያልተከፈለ የስድስት ወር ደመወዝ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረበው መልስ በቂ ተማሪዎች ባለመገኘቱና ወጪውን መሸፈን ባለመቻሉ ትምሕርት ቤቱ ስለተዘጋ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፡፡ ተጠሪ በሌለበት ደመወዝ አስወሰኑ እንጂ በክሱ የተጠቀሰው የደመወዝ መጠን ያህል አይከፈላቸውም ነበር፤ 3ኛ አመልካች ሠራተኛ አይደሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 116531 የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት መርካቶ የሚገኘው የተጠሪ ትምሕርት ቤት ቅርንጫፍ መዘጋቱ በግራቀኙ ምስክሮች የተረጋገጠ ነው፡፡ ትምሕርት ሚኒስቴርም ትምሕርት ቤቱ አገልገሎት ማቆሙን ገልጿል፡፡ አመልካቾች የሰሩት እስከ የካቲት ወር 2012 ዓ/ም ድረስ ነው፡፡ ተጠሪ በፋይናነስ ችግር፣ በኮቪድ ወረሽኝ ምክንያትና ግንቡ በመፍረሱ ምክንያት መርካቶ የሚገኘው ቅርንጫፍ የሚገኘውን ትምሕርት ቤት መዝጋቱን አስረድቷል፡፡ ስለሆነም ስንብቱ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24(4) መሠረት ሕጋዊ ነው፡፡ 3ኛ አመልካች ሠራተኛ አይደሉም፡፡ አመልካቾች ላልተሰራ ሥራ ደመወዝ መጠየቃቸው ተገቢነት የለውም፡፡ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ከገቢዎች ጽ/ቤት በቀረበው የደመወዝ መጠን መሠረት ተሰልቶ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በማከራከር ትምሕርት ቤቱ መዘጋት ስለታመነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው መባሉ ተገቢ ነው፡፡ 3ኛ አመልካች ሠራተኛ መሆናቸው ስለተረጋገጠ ክፍያዎች ይገባቸዋል፡፡ የደመወዝ መጠንን በተመለከተ ከ1ኛ-3ኛ አመልካቾች ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 113179 በተወሰነው መሰረት የ1ኛ አመልካች በወር ብር 3,500.00፣ 2ኛ አመልካች ብር 2,586.00፣ 3ኛ አመልካች ብር 5,050.00፣ 4ኛ አመልካች በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠውን ብር 3,150.00 እና 5ኛ አመልካች ብር 2,935.70 ሂሳብ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪ ሁለት ቅርንጫፍ አለው፣ መዝጋቱን ለሚመለከተው አካል ያላሳወቀ በመሆኑ በሕጋዊ መንገድ እንደተዘጋ ሊቆጠር አይገባም፡፡ ቀደም ሲል ደመወዝ እንዲከፈለን ክስ አቅርበን እስከ ግንቦት 2012 ዓ/ም ድረስ እንዲከፈለን ተወስኖ እያለ ውሳኔው ሳይለወጥ አሁን በተያዘው ጉዳይ በየካቲት 2012 ዓ/ም ነው የተዘጋው መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ሥርዓቱን የጠበቀ ስንብት ሆነ ቅነሳ አልተደረገም፡፡ የኮቪድ ስርጭት እያለ የሥራ ውል ማቋረጥ አይቻልም፡፡ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው፡፡ የደመወዝ መጠን አመልካቾች ቀደም ሲል በሌላ መዝገብ አስወሰነን እያለ የ4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች የደመወዝ መጠን ከውሳኔው ውጭ በሌላ ማስረጃ ተመስርቶ መወሰኑ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ያልተከፈለ ደመወዝ ሊከፈለን ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ተጠሪ ሥራው ያቆመበትን ምክንያት ለትምህርት ሚኒስቴር ካለማሳወቁና የኮቪድ ወረሽኝ የነበረበት ከመሆኑ አኳያ ስንብቱ ሕጋዊ ነው መባሉና ክፍያዎች የተወሰነበት አግባብነትን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ ባቀረበው መልስ ተማሪ ባለመገኘቱና ወጪውን መሸፈን ባለመቻሉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አንዱ ቅርንጫፍ ተዘግቷል፡፡ የኮቪድ ወረሽኝ ከመከሰቱ በፊት ታህሳስ 2012 ዓ/ም ላይ ነው ትምሕርት ቤቱ የተዘጋው፡፡ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፡፡ ላልተሰራ ደመወዝ ሊከፈል አይገባም፣ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብሏል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአመልካቾች የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በተጠሪ ትምሕርት ቤት ተቀጥረን ነበር፣ በ2013 ዓም ስራ እንጀምራለን ብለን ስንጠብቅ ትምሕርት ቤቱን በመዝጋት በሕገ-ወጥ መልኩ ያሰናበተን በመሆኑ ካሣ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ያልተከፈለ የስድስት ወር ደመወዝ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት እንዲከፈለን የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በቂ ተማሪዎች ባለመገኘቱና ወጪውን መሸፈን ባለመቻሉ ትምሕርት ቤቱ ስለተዘጋ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሠሪው ሠራተኛን ከሥራ ሲያሰናብት ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ይሆናል፡፡

አመልካቾች በክስ አቤቱታቸው ላይ እንደገለጹት ሆነ ተጠሪም እንዳመነው አመልካቾች የሚያስተምሩበት ትምሕርት ቤቱ መዘጋቱ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነው ተጠሪ ከአንድ በላይ ቅርንጫፍ ያለው ሲሆን የተዘጋውም ተጠሪ ድርጅት ሳይሆን አመልካቾች የሚያስተምሩበት የነበረው መርካቶ የሚገኘው ቅርንጫፍ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ድርጅት ለዘለቄታው ያልተዘጋ በመሆኑ ለጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24(4) ተፈጻሚነት የለውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀችን ማስረጃ በመስማት መርካቶ የሚገኘው የተጠሪ ትምሕርት ቤት ቅርንጫፍ በፋይናንስ ችግር፣ ግንብ በመፍረስ

ምክንያት መዝጋቱ ስለመረጋገጡ ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ይሕም ሠራተኞች የተሰማሩባቸው ሥራዎች በከፊል ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘለቄታው የሚያስቆም የሥራ ውል መቋረጥ የሚያስከትል ሁኔታ መከሰቱን ስለሚያረጋግጥ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ቅነሳው ሥርዓቱን የጠበቀ አይደለም ያሉ ሲሆን ክስ ሲያቀርቡ ቅነሳ መደረጉን መሠረት አድርገው ያልተከራከሩ ከመሆኑም በላይ ቅነሳ ለማለት በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 29(1) የተመለከተው መስፈርት ስለመሟላቱ መረጋገጥ የሚያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች (የሥራ ውላቸው የተቋረጠው የሠራተኞች ቁጥር ከአጠቃላይ የተጠሪ ድርጅት ሠራተኛ ብዛት አንጻር ምን ያህል እንደሆነ) በሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ አቅርበው ያላረጋገጡ በመሆኑ ክርክሩ በዚህ ፍርድ ቤት ደረጃ አልተቀበልነውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የኮቪድ 19 ወረሽኝ በተከሰተበት ሁኔታ ከነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና የሠራተኛ እና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከወጣው ሕግ ተጠሪ የሥራ ውል ለማቋረጥ መብት የለውም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት እንደተረጋገጠው የኮቪድ 19 ወረሽኝ አስመልክቶ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከመታወጁ በፊት ከየካቲት ወር 2012 ዓ/ም ጀምሮ የተጠሪ ትምሕርት ቤት የተዘጋ በመሆኑና የኮቪድ 19 ወረሽኝ ከተከሰተ በኂላ ትምሕርት ቤቱ የተዘጋ ቢሆን እንኳን ሥራው በሌለበት ሁኔታ አሠሪው ሠራተኞችን ይዞ እንዲቀጥል ሕጉ እንደሚያስገደድ ሆኖ ሊተረጎም ስለማይገባ የሥራ ስንብት ሕጋዊ ነው መባሉ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

በሌላ በኩል በሥር ፍርድ ቤት ለተወሰኑ ክፍያዎች የደመወዝ መጠን አስመልክቶ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ከ1ኛ - 3ኛ አመልካቾች ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 113179 በነበራቸው ክርክር ለውሳኔ መሠረት የሆነውን የደመወዘን መጠን ሲቀበል የ4ኛ እና 5ኛ አመልካቾችን የደመወዝ መጠን የቀደመውን ውሳኔ ሳይሆን በሌሎች ማስረጃዎች አረጋግጦ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል የቀረበው የሰበር አቤቱታ ለመመርመር የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ አስቀርበን እንደተመለከትነው አመልካቾች በክስ አቤቱታቸው የጠቀሱት የመዝገብ ቁጥር 113179 ሲሆን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የሚገኘውም በዚሁ መዝገብ ቁጥር ከ1ኛ-3ኛ ያሉት አመልካቾች ነሀሴ 29 ቀን 2012 ዓ/ም የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡ 4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች ከዚህ ክርክር በፊት ከተጠሪ ጋር ሌላ ክርክር ያደረጉ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት የቀረበ ውሳኔ ግልባጭ ባለመኖሩ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበለትን ሌሎች ማስረጃዎች መሠረት አድርጎ የደመወዘን መጠኑ ላይ የሠጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 250742 ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም